UK Health Security Agency


NHS

# ኤም ኤም ኣር

ኩፍኝ | ጀሮ ደግፍ | ሩቤላ









# ክትባት

ይሄ በራሪ ወረቐት ስለ ኩፍኝ፡ጀሮ ደግፍ እና ሩበላ እና ደሞ ስለ የ ኤም ኤም ኣር የሚባል ከ ሶስቱ በሽታዉች የሚከላከል ክትባትን የሚገልጽ ነዉ።

## ክትባት

ለሁሉም በማንኛዉም እድሜ ላለ ሰዉ ለመከላከል እምያግዝ

| ኤም | ኤም | ኣር |
| --- | --- | --- |
| ኩፍኝ | ጆሮ ደግፍ | ሩበላ |

## ኩፍኝ ምንድን ነው?

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ በቫይረስ የሚመጣ በሽታ ሆኖ በሳል እና ማስነጠስ ይተላለፋል።ክትባቱን ያልተከተቡ ከሁኑ እና ደሞ ይሄ በሽታ ካለዉ ሰዉ ግንኙነት ኣድርገዉ ከሆኑ፡ ይሄ በሽታ ወደ እርሶ የመተላለፍ እድሉ በጣም ከፍተኛ ነዉ።ይሄ የ ኩፍኝ በሽታ ከያዞት ደሞ በጣም ድካም ሊሰማዎት ይችላል ለ 10 ቀናቶች የሚሆን ደሞ ከ ስራም ከ ትምህርትም ሊያስቀሮት ይችላል።ለ ኩፍኝ በሽታ ደሞ ምንም ኣይነት ህክምና ወይ ደሞ መድሃኒት የለዉም።

የ ኩፍኝ በሽታ ምልክቶች ትኩሳት፡ የኣይን መቅላት እና መቁሰል እና ደሞ ሽፍታ ሊያጠቃልል ይችላል።ይሄ ደሞ ለአንዳንድ ሰዎች በጣም ከባድ የሆነ ኢንፌክሽን ሊሆን ይችላል።

የጤና ውስብስቦች በተወሰኑ ቡድኖች እንደ የተዳከመ የበሽታ መቋቋም ስርዓት ያላቸው ሰዎች፡ ከ ኣንድ ኣመት በታች ዕድሜ ያላቸዉ ህጻናት እና እርጉዝ ሴቶችን እላይ ሊያጋጥም ይችላል።እነዚ ዉስብስብ ችግሮች ደሞ የ ጆሮና ደረት ኢንፌክሽን፡መንፈራፈር፡ተቅማጥ፡ኢንሰ

ፓሊቲስ(የ አንጎል ኢንፌክሽን) እና በኣንጎል ላይ ጉዳት ሊያጠቃልል ይችላል።እነዚ ውስብስብ ችግሮች ያጋጠማቸው ሰዎች ለህክምና ሆስፒታል ዉስጥ መተኛት ሊያስፈልጋቸው ይችላል.።

ኣስጊ ነዉ ኣንዴ? ኣዎ, ኣንድ ከ 5000 ኩፍኝ የታመሙ ሰዎች የ ሞት ኣደጋ ሊያጋጥመዉ እሚቹል ሲሆን ከ 2006 ኣመተ ምህረት ጀምሮ በ ኢንግላንድ እና ዌልስ 3 ሰዎች በዚ ህመም ሞተዋል።

## ጀሮ ደግፍ ምንድን ነው?

ጀሮ ደግፍ በ ቫይረስ የሚመጣ ህመም ሆኖ በሳል እና ማስነጠስ እናም የ ጀሮ ደግፍ በሽታ የተጠቃ ሰዉ ጋራ ቅርብ ግንኙነት በማድረግ ሊተላለፍ ይችላል።

የ ጀሮ ደግፍ ምልክቶች ብዙ ግዜ እስከ ሁለት ሳምንታን የሚቆይ ሆኖ ትኩሳት እና የራስ ህመም ሊያጠቃልል ይችላል፡ ግን ደሞ ብዙ ግዜ የሚታየዉ ምልክት ፊታችን ላይ በጎን ያሉትን እጢዎችን ማበጥ ነዉ።እሄ ደሞ የ ሃምስተር ፊት የሚመስል እብጠት ያለዉ ፊት እንዲኖርክ ያረጋል እናም ህመም ሊያረክ ይችላል እና ለ መዋጥ ሊያስቸግር ይችላል።

የጤና ውስብስቦች የ ጀሮ ደግፍ የጤና ውስብስቦች ብርቱ ሊሆን ይችላል እናም የ ማሃጸን እና የ ዘር ፍሬን እብጠት በተወሰነ ግዜያት ደሞ የ ቆሽት ማበጥ ወይ መቁሰል ሊያስከትል ይችላል። ከዚ በተጨማሪ ደሞ ጀሮ ደግፍ በቫይረስ የሚመጣ መኒንጃይትስን ኢንሰፕሃሊቲስ (የ አንጎል ኢንፌክሽን) ሊያስከትል ይችላል። ምንም እንኳን የመስማት ችሎታክን በቀዋሚነት ሊያጠፋው የሚችልበት (በቀዋሚነት መደንቆር) ኣጋጣሚ ብዙ ባይሆንም፡ 1 ከ 20 በ ጀሮ ደግፍ የተጠቁ ሰዎች ግዝያዊ የጀሮ መደንቆር ሊያጋጥማቸዉ ይችላል።

እስከ ኣሁኑ ግዜ ጀሮ ደግፍ ለመፈወስ የሚያስችል መድሃኒት የለም፡ ስለዚ ደሞ የ ጀሮ ደግፍ ፍወሳ ለሚታዩ ምልክቶችን እንዲረጋጉ በማድረግ ነው የሚፈጸም። ጀሮ ደግፍ በሽታ ከያዘክ ኣልጋ እላይ እረፍት እና የህመም ማስታገሻ መድሃኒት መውሰድንም ሊያስፈልግዎት ይችላል። እናም ቀለል ያለ እና ብዙ ማኘክ የማያስፈልገዉ የምግብ ኣይነት ሊያስፈልጎት ይችላል። በዚ ግዜ እየታየ ያለዉ የ ጀሮ ደግፍ በሽታ በብዛት ሁለቱንም የ ኤሚ ኤም ኣር ክትባት ባልወሰዱት ታዳጊ ወጣቶች እላይ ነዉ እየታየ ያለዉ።

## ሩቤላ ምንድን ነው?

ሩቤላ በ ቫይረስ የሚተላለፍ በሽታ ሆኖ ብዙ ግዜ የ ጀርመር ኩፍኝ ተብሎም የሚጠራ ነዉ። ምስጋና ለ ስኬታማነት የ ኤምኤምኣር ክትባት ሩቤላ በ  ታላቋ ብሪታኒያ ብዙም ኣይታይም። ልክ እንደ ኩፍኝ እና ጀሮ ደግፍ በተመሳሳይ መንገድ ይተላለፋል። ብዙ ሰዎች እላይ ደሞ መካከለኛ እሚባል ሁኔታ የሚያስከትል ሆኖ ያለ ምንም ህክምና ከ 7 እስከ 10 ቀናቶች ባለ ግዜ በራሱ የሚያገግም ነዉ።ሆኖም ግን፡ነብሰጡር እናቶች ሩቤላ ከታየባቸዉ ሆዱዋ ዉስጥ ላለው ያልተወለደዉ ህጻን በጣም ኣደገኛ ነዉ።

የ ሩቤላ ምልክቶች እንደ ሽፍታ፣ ጉንፋን የሚመስል ምልክቶች እና በጣም ህመም ያለዉ መገጣጠምያዎች ያጠቃልላል።

የጤና ውስብስቦች የ ሩቤላ ብዙ የተለመድ እንኳን ባይሆንም ነብሰጡር እናቶች በ እርግዝና ግዜያቸዉ ሩቤላ ከያዛቸዉ ደሞ ላልተወለደዉ ህጻኑ በጣም ኣደገኛ ሊሆን ይችላል፡ ህጻኑ ሲወለድ የዓይን ሞራ ግርዶሽ (የዓይን

ችግሮች) : የ ጆሮ መዶንቆር፡ የ ልብ
ችግሮች እና ጉዳት ኣንጎል ላይ ይዞ
ሊወለድ ይችላል።

1

## ኣንድ ክትባት

ክትባት ኤም ኤም ኣር ኣንድ መርፌ ሆኖ ትናንሽ ልጆች ላይ በጭናቸዉ እላይ ትላልቅ ልጆች እና ጓልማሶች እላይ ደሞ የላይኛው ክንዳቸዉ,ጋ እሚወጉት ነዉ። ይሄ ክትባት ደሞ ህያዉ ክትባት ነዉ ይሄ ማለት ደሞ የተዳከሙ ስረቶች የ ኩፍኝ፡ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላን ቫይረስ ያለዉ ነዉ። እነዚ ደሞ በሽታ ሊያስከትሉ እማይችሉ የተዳከሙ ስረቶች ሆኖዉ ሰዉነታችን ደሞ ለንደዚ ኣይነት ቫይረስ የ መከላከል ኣቅም ኣንዲያጎለብት ያስችለዋል።

2

## ሁለት ክትባት

ክትባት ኤም ኤም ኣር ሁለት ክትባት ከወሰድን ነዉ ለ ረጅም ግዜ የሚቆይ የመከላከል ኣቅም ሊሰጠን የሚችለዉ። ያቺ የመጀመርያ ክትባት በ 12ኛዉ ወር ዕድሚያችን የምትሰጥ ሆና ሁለተኛዋ ክትባት ደሞ በ 3 ዓመት ከ 4 ወር ዕድሜያችን ይወሰዳል፡ ይሄ ደሞ ትምህርት ከመጀመራችን በፊት ነው። ሁለቱ ክትባት ከወሰድን ደሞ ለ ረጅም ግዜ የሚቆይ ለ ንፍዮ፡ጽግዕን ፍሮማይን በሽታዎች የመከላከል ኣቐም ይሰጠናል። በ ትላልቅ ልጆች እና ጓልማሳ ሰዎች እነዚ ሁለት ክትባቶች የኣንድ ወር የግዜ ልዩነት በማድረግ ሊወሰዱ እሚችሉ ናቸዉ።

3

## ሶስት ኢንፌክሽኖች

ክትባት ኤም ኤም ኣር ከሚከተሉት ሶስት ኢንፌክሽኖች ይከላከላል፡ ኩፍኝ፡ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ። እነዚ ደሞ በ ቫይረስ የሚተላለፉ ሆነዉ በ ያልተከተቡ ልጆች እና ጎልማሳ ሰዎችን እላይ በጣም ተላላፊ ነው፡ ከ ኢንፉለንዛ እና ጉንፋን በላይ በቀላል ሊተላለፍ ይችላል።

»

## ለረጅም ግዜ የሚቆይ የመከላከል ኣቅም

ክትባት ኤም ኤም ኣር በጣም አስተማማኝ እና በጣም ውጤታማ የሆነ እራስህን ከ ኩፍኝ፡ጆሮ ደግፍ ሩቤላን በሽታዎች እምትከላከልበት መንገድ ነው። ይሄ  ክትባት በ 1988 ኣመተ ምህረት ሊሰጥ ከጀመረ ጀምሮ በ  ታላቋ ብሪታንያ እነዚ በሽታዎች በብዛት እየታዩ

ኣይደሉም።እሄ ሆኖም እያለ ግን ይሄንን ክትባት የሚወስዱት ሰዉች ቁጥር ግን እየቀነሰ ሲሄድ የነዚ በሽታዎች በተለይ ደሞ የ ኩፍኝ ወረርሺኝ ታይቶ ነበር። ካሁን በፊት ይሄንን ክትባት መዉሰድህን ወይ ኣለመዉሰድህን እርግጠኛ ካልሆክን ለ ሃኪምህን ጠይቀዉ፡ እሄ ሆኖም እነዚ ክትባቶች ደግመክ መዉሰድ ምንም ኣይነት ጉዳት የሚያስከትል ኣይደለም።

# ማን ነዉ እነዚ ክትባት መከተብ ያለዉ?

## ትናንሽ ልጆች

ትናንሽ ልጆች በ ብሔራዊ የ ታላቋ ብሪታንያ የክትባት መርሃ ግብር መሰረት ይሄንን ክትባት ሊሰጣቸዉ ይገባል።ሁለት ክትባት ደሞ ሊሰጣቸዉ ነዉ፡ የመጀመርያዋ ክትባት ዕድሜያቸዉ ኣንድ ኣመት ከሞላቸዉ ብሁዋላ የሚሰጥ ሆኖ ሁለተኛዋ ክትባት ደሞ ትምህርት ከመጀመራቸዉ በፊት በዙ ግዜ እድሚያቸዉ 3 ኣመት ከ 4 ወር ኣከባቢ ሲደርስ ይሰጣሉ።

## ትልልቅ ልጆች፣ ጎረምሶች እና ጎልማሶች

ካሁን በፊት ክትባት ኤም ኤም ኣር ያልተከተብክ ወይ ደሞ ኣንድ ክትባት ብቻ ተከትበክ ያቺ ሁለተኛዋ ያልተከተብክ ከሆንክ፡ ቀርቶክ ላለዉ ክትባት ለመዉሰድ ለ ሃኪምክን ኣናግረው። ካሁን በፊት ትንሽ ልጅ ሆነክ ኣንድ ክትባት ኤም ኤም ኣር ወስደክ ከሆንክ ኣሁን ሁለተኛዋ ክትባት ብቻ ነዉ የምትወስደዉ ኣንደኛዉ ክትባት ከወሰድክ ምንም ያህል ግዜ ቢሆንህም።ሁለቱ ክትባት የሚያስፈልግክ ከሆነ ደሞ የ ኣንድ ወር የግዜ ልዩነት በማድረግ ሁለቱም ክትባት መዉሰድ ይችላሉ።

## ልጅ መዉለድ በሚችሉበት እድሜ ላሉ ሴቶች

ሩቤላ ላልተወለደ ህጻን በጣም ኣደገኛ ኢንፌክሽን ሊሆን ይችላል። ዓይነ ስውርነት፡ የጆሮ መዶንቆር ከዛም ብሶ ሞት ሊያስከትል ይችላል። ልጅ መዉለድ በምትችይበት እድሜ ያለሽ ሴት ከሆንሽ፡ ልጅ የመዉለድ እቅድ ባይኖርሽም ከማርገዝሽ በፊት ሁለት ክትባት የ ኤም ኤም ኣር መከተብ ኣለብሽ። ሁለቱን ክትባት ካልወሰድሽ ወይ ደሞ ሁለቱን ክትባት መዉሰድሽ እርግጠኛ ካልሆንሽ ደሞ ሃኪምሽን ኣነጋግረሽ የቀረሽን ክትባት መዉሰድ ኣለብሽ። ይሄ ክትባት ህያዉ ክትባል ስለ ሆነ ደሞ ከመከተብሽ ቡኋላ ለ ኣንድ ወር ከ ማርገዝ ተቆጠቢ ስለዚህ በዚህ የ ኣንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስተማማኝ የእርግዝና መከላከያ ዘዴን መጠቀም አለብሽ። ነብሰጡር ወይ ደሞ በቅርብ የወለድሽ ኣራስ ከሆንሽ እና ይሄንን ሁለት የ ኤም ኤም ኣር ክትባት መዉሰድሽን እርግጠኛ መሆን ካልቻልሽ ደሞ ለ ሃኪምሽ ወይ ለ ነርስ ከመዉለድሽ ቡኋላ ከ 6 ሳምንታት ሁኋላ ከነሱጋሩ ባለሽን ቀጠሮ ላይ ንገሪያቸዉ።

## ትላልቅ አዋቂዎች

ከ 1970 ኣመተ ምህረት በፊት በ ታላቋ ብሪታንያ የተወለዱ ሰዎች ኩፍኝ፡ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላን በሽታዎች ባለፈ ዘመናቸዉ ታመዉ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ ደሞ ኤም ኤም ኣር በ 1988 ኣመተ ምህረት ሊሰጥ ከመጀመሩ በፊት የሚሰጥ የነበረዉን ኣንድ ክትባት የ ኩፍኝ ወይ ሩቤላ ተከትበዉ ሊሆኑ ይችላሉ። ካሁን በፊት እነዚን በሽታዎች ታመክ መኖርክ ወይ ደሞ ክትባቱን

መከተብህን ወይ ኣለመከተብህን እርግጠኛ መሆን ካልቻልክ ለ ሃኪምህን እነዚን ክትባቶች እንዲሰጥክ ኣናግረዉ። ሁለት ክትባት መዉሰድ ያስፈልግሃል የ ኣንድ ወር የ ግዜ ልዩነት በማድረግ ደሞ ሁለቱን ክትባት ይወሰዳሉ። እነዚ ክትባቶች ካሁን በፊት ወስደዉት ከሆኑ እንኳን ድጋሜ ሲወስዱት ሰዉነትዎ እነዚን ቫይረስ ስለሚያቃቸዉ እና ደሞ በፍጥነት ስለሚገድላቸዉ ምንም ጉዳት የሚያከትል ኣይደለም።

## ሌላ ሃገር ከተወለዱ ወይደሞ ከ ሌላ ሃገር ከመጡ?

በ ሌላ ሃገር ከተወለድክ ወይ ደሞ ከ ሌላ ሃገር ከመጣክ ሁለት ክትባት ኤም ኤም ኣር ሊያስፈልጎት ይችላል። የተለያዩ ሃገሮች የተለያየ የክትባት መንገድ ይከተላሉ በዛላይ ደሞ ሁሉም ሃገሮች ሁለት የ ኤም ኤም ኣር ክትባት ኣይጠቀሙም። የተከተብክበት መዝገብ ወረቀት ከሌለክ ወይ ደሞ እርግጠኛ ካልሆንክ ከ ሃኪምህ ጋራ ተነጋገር፡ እሄ እንዳለም ከ ሌሎች በሽታዎች የሚከላከሉልክ ሌላ ክትባቶች ሊያስፈልጉክ ይችላሉ።

## የ ኤም ኤም ኣር ክትባት እንዴት ነዉ የሚሰራዉ?

ክትባት ኤም ኤም ኣር ህያዉ ክትባት ሆኖ ከ ኩፍኝ፡ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ የሚከላከል ነዉ።ሁለት ክትባቶች ሆነዉ እግር ላይ ወይ ደሞ በላይኛዉ ክንድ ላይ የሚወጉት ነዉ። የ ሰዉነታችን በሽታ የመከላከል ስርኣት ደሞ ለነዚ ሶስት ቫይረስ የሚያዉቁዋቸዉ እና የሚያስታዉስዋቸዉ ሕዋሳት በማምረት መልስ ይሰጣል። ወደፊት ደሞ ወደ እነዚ በሽታዎች ከተጋለጡ፡ እነዚ ሕዋሳት ይነሱ እና ሰዉነትዎ ደሞ በጣም በፍጥነት ጸረ ነፍሳት (ለመከላከል የሚያስችሉ) ያመርታል። እነዚ ደሞ ለረጅም ግዜ የመከላከል ኣቅም ይሰጣል።



## ክትባቱ ምን ያህል ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።?

ለብዙ ኣመታት በ ብዙ ሃገራት ኣለም ሁለቱ ክትባት ኤም ኤም ኣር ለልጆች ደህንነቱ የተጠበቀ የ መከላከል ኣቅም አየሰጣቸዉ ይገኛል። በ ታላቋ ብሪታንያ፡ በ 1988 ኣመተ ምህረት መሰጠት ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ በ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ክትባት ተሰጥተዋል። ክትባቶች ጥቅም ላይ ከመዋላቸዉ በፊት የ ዋስትና ፈተና ይደረግላቸዋል። ምንም እንኳን ኣንድ ኣንድ የ የጎንዮሽ ጉዳቶች ቢኖራቸዉ፡ ብዙ ግዜ የሚታየዉ የጎንዮሽ ጉዳት መካከለኛ እና እራሱ በሽታዉ ከሚያስከትለዉ የጤና እክል በጣም የተሻለ ነዉ። ከ ክታበቱ ቡኋላ በሰዉነታችን የሚታይ ከባድ የጎንዮሽ ምልክቶች የመከሰት እድል በጣም ትንሽ ነዉ።

የ ኤም ኤም ኣር ክትባት ዋስትና እና ዉጤታማነት ለማረጋገጥ በጣም ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል። ያሉት ማስረጃዎች እሚያሳዩት ደሞ ክትባት ኤም ኤም ኣር ከ ኦቲዝም ጋራ ምንም ተያያዥነት እንደሌለዉ ነዉ።

## ግን ይሰራል?

ኣዎ፡ ይሄ ክትባት ለ ኩፍኝ፡ ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላን መከላከል ላይ በጣም ዉጤታማ ነዉ።

ሁለቱም ክትባት የወሰዱ ሰዎች ከ 99% በላይ ለ ኩፍኝ እና ሩቤላን የመከላከል ኣቅም ኣላቸዉ፡ ለ ጆሮ ደግፍ በሽታ ደሞ ምንም እንኳን ዝቅ ያለ ቢሆንም በተከተቡ ሰዎች ላይ የ ህመም ስሜት ግን በጣም የተሻለ ነዉ። ኤም ኤም ኣር በ 1988 ነዉ በታላቋ ብሪታንያ መሰጠት የጀመረዉ፡ ኣሁን በዚ ግዜ ደሞ ልጆች በነዚ በሽታዎች ሲጠቁ ብዙ ኣይታዩም። ከ ቅርብ ኣመታት በፊት የ ኩፍኝ እና ጆሮ ደግፍ ወረርሺኝ ታይቶ ነበር።ይሄ ደሞ ክትባቱን የሚከተቡት ሰዎች ቁጥር ከቀነሰ ብኋላ የታየ ወረርሺኝ ነዉ፡ ሆኖም ግን ይሄ ወረርሺኝ በ ማንኛዉም ግዜ ሊታይ ስለ ሚችል ሰዉነትህን ሁለቱም የ ኤም ኤም ኣር ክትባት ወስዶ ተገቢ የመከላከል ኣቅም ማዳበሩን ኣረጋግጥ።

## የዚ ክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶች ምንድናቸዉ?

ሁሉ የተከተበ ሰዉ የጎንዮሽ ጉዳት ያሳያል ማለት ኣይደለም። ተገቢ የመከላከም ኣቅም ለመስጠት፡ ይሄ ክትባት ለነዚ 3 ልንከላከላቸዉ ፈልገን ያለን ኢንፌክሽኖች ሰዉነታችን ዉስጥ ኣስመስሎ እንደ ሚፈጠሩ ያደርጋል። በ ኣንድ ኣንድ ሰዎች ደሞ ሽፍታ የሚመስል ቀለል ያለ ኩፍኝ፡ የ ፊታችን ማበጥ (ጆሮ ደግፍ የሚመስል) እና ደሞ የ ኣሰዉነታችን መገጣጠሚያዎች ላይ የ ህመም ስሜት እና ሩቤላ የሚመስል ሊታይ ይችላል። እነዚ የጎንዮሽ ጉዳቶች በ ትንሽ ሰዎች የ መጀመርያዉን ክትባት ከወሰዱ ቡኋላ ይታያል።

ብዙ ግዜ የከታበቱን የ ኩፍኝ ክፍል
ጎንዮሽ ጉዳቶች በ 6 እስከ 10 ቀናቶች
ከ ክትበቱ መዉሰድክ ቡኋላ ክትበቱ
ስራዉ ከጀምረ ቡኋላ ነዉ የሚታየዉ። የ
ፊት እብጠት ወይ ደሞ ህመም የ
ሰዉነታችን መገጣጠምያዎች ላይ በ 2
እስከ 3 ሳምንታት ከክትባቱን ቡኋላ ያ የ
ሩቤላ እና ጆሮ ደግፍ የክትባቱን ክፍል
ስራዉን መስራት ሲጀምር ነዉ
የሚታየዉ።

የ ጎንዮሽ ጉዳቶች እንደ ሽፍታ፡የ ኣንገታችን ማበጥ 2 እስከ 3 ቀናቶች የሚቆይ እና ደሞ የማይተላለፍ ነዉ። ይሄ ማለት ደሞ እነዚ ምልክቶች የ ጎንዮሽ ጉዳቶች ሰዉነትክ ዉስጥ ከታዩ ወደ ሌላ ሰዉ ሊተላለፉ ኣይችሉም ማለት ነዉ።

በተወሰኑ አጋጣሚዎች፡ ቀይ ወይ ሃመር ቀለም ያለዉ ጥቃቅን ቁስሎች የሚመስል ሽፍታ ከ ክትባቱ ቡኋላ እስከ 6 ሳምንታት ሊታይ ይችላል።

ክትባት መዉሰድ ኣለቦት።

ኩፍኝ ወደ የ ኤም ኤም ኣር ክትባት መዉሰድ የማይችሉ ህጻናትን ወይ ደሞ የጤና ችግር ያለባቸዉ ሰዎችን ከተላለፈ ደሞ በጣም ከባድ የጤና መዘዝ ሊያስከትል ይችላል።
እንደ ማስጠንቀቅያ፡ ሴቶች የ ኤም ኤም ኣር ክትባቱን ከወሰዱ ቡኋላ እስከ ኣንድ ወር እርግዝና እንዳይዙ መጠንቀቅ ኣለባቸዉ።

## ለምን እኔ ወይ ልጆቼን ለዚ ክትባት እንከተበዋለን?

ለራስዎ ከእነዚ 3 ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል ይሄ ክትባት መከተብ ኣለቦት።ይሄ ክትባት በመከተባቸዉ ደሞ ለሌሎች ክትባቱን መዉሰድ እማይችሉ ሰዎች ጭምር ልትከላከልላቸዉ እሚያስችልክ ነው። እነዚ ሰዎች ደሞ ያልተወለዱ በርግዝና ላይ ያሉ ህጻናት፡ ለዚ ክትባት ለመውሰድ እድሚያቸዉ ያልደረሰ ጨቅላ ህጻናት እና ደሞ ደካማ የሰዉነታቸውን የመከላከል ስርኣት ያላቸዉ  ልጆች ወይ ኣዋቂዎች ናቸዉ። ይሄ ደሞ የእነዚ በሽታዎች ወረርሺኝ እንዳያጋጥም ያግዛል።



ከ ትናንሽ ልጆች ጋራ የምትሰራ ከሆንክ ወይ ደሞ ሌሎችን መንከባከብ ላይ እምትሳተፍ ከሆንክ ደሞ ይሄ

## ክትባት ኤምኤምኣር ገላቲን ኣለዉ ወይ?

በ ታላቋ ብሪታንያ፡ ሁለት በጣም ዉጤታማ የ ኤም ኤም ኣር ክትባት ኣሉ።
ኣንዳቸዉ ገላቲን የሚባል ከ ኣሳማ የሚገኝ ፕሮቲን ንጥረ ነገር ሲኖሮው ሁለተኛዉ ኣይነት ደሞ ይሄ ገላቲን እሚባል ፕሮቲን የሌለዉ ነዉ።
ያ ገላቲን ፕሮቲን የሌለዉ ክትባት መዉሰድ ከፈለግክ ለ ነርስ ወይ ደሞ ለ ሃኪምክ ያማክሩአቸው።

ኡፍኝ፡ ጀሮ ደግፍ እና ሩበላ ይዞኝ ይሆናል ብለዉ ካሰቡ፡ ወደ ሌሎች ሰዉች እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ማድረግ ኣስፈላጊ ነዉ። ማረግ ያለቦት ደሞ፡

- ምክር ለማግኘት ለ ሃኪምክ ደዉልለት፡ ምናልባት በቀኑ በ መጨረሻ ሰኣታት ወደ ህክምና መጥተክ እንድታገኘዉ ሊያረግ ይችል ይሆናል። ይሄ ሚደረገዉ ደሞ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት ሰዎች እንደ ትናንሽ ልጆች እና ነብሰጡር እናቶች ታካሚዎች መነካካት እንዳይፈጠር እና በሽታዉ እንዳይተላለፍ ነዉ።
- ይሄ ምልክቶች መታየት ከ ጀመረበት ግዜ ጀምረክ ከ ስራም ትምህርትም በትንሹ ለ 4 ቀናቶች ኣቛርጥ።
- ከ በሽታዉ ካገገምክ ቡኋል ደሞ ቀርቶክ ላለው ክትባቶችክን ለመዉሰድ ዝግጅት ኣድርግ፡ ይሄ ክትባት መዉሰድ ደሞ ከሊሎች ሁለቱ በሽታዎች ይከላከልልሃል።

## ክትባት ኤምኤምኣር መከተብ የሌለባቸዉ ሰዎች ኣሉ ወይ?

ክትባት ኤም ኤም ኣር ህያዉ ክትባት ስለ ሆነ ለነብሰ ጡር እናቶች እና ለ ደካማ በሽታ የመከላከል ስርዓተ ሰዉነት ያላቸዉ ሰዎች ለምሳሌ የ ኣጥንት መቅን የተተከለላቸዉ ሰዎችን ወይ ደሞ የ ሰዉነታቸዉን በሽታ የመከላከል ስርኣትን ለመቀነስ መድሃኒት የሚወስዱ ሰዎች ክትባቱን መሰጠት የለበትም።

እርግጠኛ ካልሆንክ ከ ሃኪምክ ጋራ ተነጋገር። ሰዉነትክ ኔኦምይሲን የሚባል መድሃኒት ከተጠቀምክ ኣናፊላክቲክ የሚባል ኣለርጂ እንደምታዳብር ከተረጋገጠልክ ይሄ ክትባት መከተብ የለቦትም። ሰዉነትክን ገላቲን ከወሰድክ ኣናፊላክቲክ የሚባል ኣለርጂ እንደሚያሳይ ከተረጋገጠልክ ከ ሃኪምክ ጋራ ተነጋግረክ ከ ገላቲን ነጻ የሆነ ክትባት መከተብ ኣለብክ።

## የ እንቁላል ኣለርጂ

ሁሉም የ እንቁላልኣለርጂ ያላቸዉ ሰዎችን እና እስም ያላቸዉ ልጆችን ጨምሮ ይሄ ኤም ኤም ኣር ክትባት በ ጂፒ ሕክምና መከተብ የሚችሉ ናቸዉ። ምንም ኣይነት ለ ኤም ኤም ክትባት ከወሰዱ ኣናፎላክቲክ ኣለርጂ ኣንዳላቸዉ የሚገልጽ ዶኩመንት ካላቸዉ በየኣለርጂ ሃኪሞዎት መመርመር ኣለቦት።

# ምልክቶቹ ምንድ ናቸዉ?

| ኩፍኝ | ጆሮ ደግፍ | ሩበላ |
| --- | --- | --- |
| ትኩሳት፡ የ ጉንፋን ምልክት፡ ሽፍታ፡የቆሰለ ወይ የቀላ ኣይን | ትኩሳት፡ የጭንቅላት ህመም እና ፊትዎ እላይ ያበጡ እጢዎች | ያበጡ እጢዎች፡የጎሮሮ ህመም፡ትኩሳት እና ሽፍታ |

## ከቢድ ነገር ድዩ?

| | | |
| --- | --- | --- |
| **ኣዎ** | **ኣዎ** | **ኣዎ** |
| 1 ከ 5 የታመሙ ሰዎች ወደ ሆስፒታል ይሄዳሉ፡ 1 ከ 15 ደሞ ከባድ የጤና ውስብስብነት ያስከትልላቸዋል። ኩፍኝ የ ጆሮ መደንቆር፡መንፈራፈር፡ኣ ንጎል ላይ ጉዳት፡ የ ኣንጎል እብጠት ሊያመጣ ይችላል።በ ታላቋ ብሪታንያ ከ 2006 ጀምሮ 3 ሞት በ ኩፍኝ ታይቶዋል። | ምንም እንኳን ብዙ ግዜ ምልክቶቹ መካከለኛ ቢሆኑም፡ ጆሮ ደግፍ እንደ ተላላፊ መኒንጃይትስን እና እብጠት/ህመም የ ማህጸን ወይ የዘር ፍሬ በጣም ኣልፎ ኣልፎ ደሞ የቆሽትን ሊያስከትል ይችላል። | ምንም እንኳን ምልክቶቹ መካከለኛ ቢሆኑም፡ ሩቤላ በሽታ በ እርግዝና ግዜ ካጋጠመ ላልተወለደዉ ህጻን ጉዳቱ ከባድ ሆኖ እንደ የጆሮ መዶንቆር፡ ዓይነ ስዉርነት ከዛ ብሶም ሞት ሊያስከትል ይችላል። |

## ማን ነዉ እነዚ ክትባት መከተብ ያለባቸዉ?

- ሁሉም ከ 1 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸዉ ልጆች 2 ክትባት መዉሰድ ኣለባቸዉ፡ የመጀመርያዉ ክትባት በ ኣንድ ኣመት እድሜያቸዉ መወሰድ ያለበት ሆኖ ሁለተኛዉ ክትባት ደሞ ብዙ ግዜ በ ሶስት ኣመት ከ ኣራት ወር እድሜያቸዉ ይከተቡታል።
- ትላልቅ ልጆች እና ኣዋቂ ሰዎች ሁለቱ ክትባት መዉሰድ ኣለባቸዉ ይሄ ክትባት ደሞ የ ኣንድ ወር የግዜ ልዩነት ኣርገዉ መከተብ ይችላሉ።
- ነብሰ ጡር እናቶች እርግዝና ከመያዛቸዉ በፊት ይሄንን ክትባት ተከትበዉ መሆናቸዉን እርግጠኛ መሆን ኣለቦት ወይ ደሞ ከ ወሊድ ቡኋላ በ ኣጭር ግዜ መከተብ ኣለባቸዉ።

**ሁለቱም ክታበት ኣልፎኛል ሳትል በየትኛዉም ግዜ መከተብ ይቻላል**

## ይሄ ክትባት የት ላገኘዉ እችላለዉ?

### በ ጂፒ ሕክምናክ

- ሁሉም ከ ኣንድ ኣመት እስከ ሶስት ኣመት እና ኣራት ወር እድሜ ያላቸዉ ልጆች በ መደበኛ ክፍል የ ክትባቶቹን በ ጂፒ ህክምና ሊሰጣቸዉ ይገባል።
- ትላልቅ ልጆቹ እና ኣዋቂ ሰዎችን ኣንድ ክትባት ብቻ ተከትበዉ ከሆኑ ወይ ደሞ ምንም ያልተከተቡ ከሆኑ ለ ጂፒ ህክምናዎ ማናገር ኣለቦት።
- ሁለቱ ክትባት ያልወሰደች ነብሰ ጡር እናት ከ ወሊድ ቡኋላ በ ጂፒ ህክምናዎ ይሄንን ክትባት መዉሰድ ኣለባት።

### ትምህርት ቤት ዉስጥ

ኣንድ ኣንድ ጎረምሳዎች እና ወጣት ጎልማሶች ላለፉቸዉ የ ኤም ኤም ኣር ክትባት ከሌሎች ልጆች ጋሩ ሊሰጣተዉ ይችላል።

### ከ ኣሰሪዎ የ ስራ የጤና ኣገልግሎት

የ ጤና ኣገልግሎት ሰራሕተኛዎች ቀጥታዊ ግንኙነት ከ ታማሚዎች ጋሩ ያላቸዉ ከሆኑ ይሄ የ 3 በሽታዎች ክትባት መዉሰዳቸዉ እርግጠኛ መሆን ኣለቦት።

# ኩፍኝ፡ ለልጆች ብቻ የሚመለከት በሽታ ኣይደለም

ስለ ኤም ኤም ኣር ክትባት ከዚህም በላይ መረጃ ከፈለጉ በዚ ቀጥሎ ባለ ወብሳይት ይመልከቱ
www.nhs.uk/conditions/vaccinations/pages/mmr-vaccine.aspx

© ክራዉን የቅጂ መብት 2022
3219250 2p 75K MAR 2020
(APS)

የመጀመርያ ቅጂ ሰኔ 2016

ይሄ ጽሑፍ የዚ ወረቐት ያለ ፍቃድ ወይ ክፍያ ለ ግላዊ ወይ ለ ቤት ዉስጥ ፍጆታ ሊባዛ የሚችል ነዉ

ሌላ ቅጂ የዚ ወረቀት ከፈለጉ በዚ ቀጥሎ ባለ ወብሳይት ይመልከቱ
www.healthpublications.gov.uk/Home.html ኮድ ናይ
ፍርያት: 3219250 ወይ ቴሌፎን: 0300 123 1002,
ሚኒኮም: 0300 123 1003 (8 ጥዋት እስከ 6 ከሰኣት, ሰኞ እስከ ኣርብ)

www.nhs.uk/vaccinations